የ CAMBRIDGE ከተማ
Community Development Department (የማኅበረሰብ ዕድገት ክፍል)

**IRAM FAROOQ**
*የማህበረሰብ ልማት ረዳት የከተማ አስተዳዳሪ*

**SANDRA CLARKE**
*የአስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር*

**KHALIL MOGASSABI**
*የእቅድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር*

ሜይ 18፣ 2023

ውድ የ Cambridge የቢዝነስ ባለቤት፦

የ Cambridge ከተማ በ Cambridge ትንንሽ ንግዶች ላይ የ Cycling Safety Ordinance (የብስክሌት ደህንነት ድንጋጌን) ተከትሎ በተፈጠሩ የብስክሌት መገልገያዎች ምክንያት የትራፊክ ለውጦችን ተፅእኖ ለመገምገም የ Economic Impact Study (ኢኮኖሚ ተፅእኖ ጥናት) እያካሄደ ነው። በዚህ ጥናት ላይ ከዩናይትድ ስቴትስ Department of Transportation's (የትራንስፖርት ክፍል) የ Volpe ብሔራዊ የትራንስፖርት ስርአት ማእከል ጋር እየሰራን እንገኛለን። ጥናቱ በሕገ ደንቡ ተጽዕኖ በሚደርስባቸው ኮሪደሮች ማለትም ከቸርቻሪዎች እና ከግለሰቦች እና ከህክምና አገልግሎት ንግዶች ውስጥ ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን እና የንግድ ተፅእኖ መረጃዎችን መሰብሰብን ያካትታል።

**የቢዝነስ የዳሰሳ ጥናት**

በኢንተርኔት ቀጥታ መስመር የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ቸርቻሪዎችን፣ ምግብ ቤትን፣ ግለሰቦችን እና የህክምና አገልግሎት ሥራዎችን እንጠይቃለን። የዳሰሳ ጥናቱ ከ 5-6 ደቂቃዎችን ይወስዳል። ከ Cambridge ንግዶች ትክክለኛ የሽያጭ መረጃ ማግኘት እንድንችል እባክዎ የዳሰሳ ጥናቱን ይመልሱ እና የንግድዎን የፋይናንስ መረጃን ያካፍሉን። ትክክለኛውን የኢኮኖሚ ተጽእኖ ምስልን ለማግኘት፣ ከንግድ ተቋማት የፋይናንስ መረጃን ማግኘት በጣም ጠቃሚ ነው። የዳሰሳ ጥናቱ የ Cambridge የንግድ ተቋማትን በፈቃደኝነት የገንዘብ መረጃቸውን ከእኛ ጋር እንዲጋሩ መጠየቅንም ያካትታል። **እርስዎ ያቀረቡት የፋይናንስ መረጃ በሕግ እስከ ተፈቀደው ድረስ በሚስጢራዊነት የሚጠበቅ ሲሆን መረጃው የሚጋራው በድምሩ ብቻ ይሆናል።**

ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ የፋይናንስ መረጃ ናሙና ዓይነቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- ሽያጮች/የምግቦች የግብር መረጃ
- የግብር ተመላሾች
- የትርፍ እና የኪሳራ መግለጫዎች

**ይህ የዳሰሳ ጥናት መሞላት ያለበት በንግዱ ባለቤት፣ ስራ አስኪያጅ ወይም የንግዱን እንቅስቃሴ እና ፋይናንስ እውቀት ባለው ሰው ነው።** በ Cambridge ውስጥ የበርካታ ንግዶች ባለቤት ከሆኑ፣ እያንዳንዱ ቦታ ልዩ የሆነ የዳሰሳ ጥናት ማስፈንጠሪያ ይደርሰዋል።

**ልዩ የሆነው የዳሰሳ ጥናት QR ኮድ የሚሰራው ለንግድዎ ብቻ ነው።** ከከተማው ደብዳቤ አልደረሰም ብለው የሚያምኑት የቢዝነስ ጎረቤት ከአለ፣ ስለ ጥናቱ ጥያቄዎች ከአልዎት፣ ወይም ከታች ያለውን ማስፈንጠሪያ ማግኘት ላይ ችግር እያጋጠምዎት ከሆነ፣ እባክዎን በ edd@cambridgema.gov ያግኙን እና አንድ ሰው እርዳታ ያቀርብልዎታል።

ከሰላምታ ጋር፣

Pardis Saffari
የኢኮኖሚ ዕድል ተጠቃሚነት እና ዕድገት ዳይሬክተር
የ Cambridge ከተማ፣ Community Development Department

344 Broadway
Cambridge, MA 02139
ስልክ፦ 617 349-4600
ፋክስ፦ 617 349-4669
ነጻ የስልክ መስመር፦ 617 349-4621
www.cambridgema.gov

## Cycling Safety Ordinance ምንድን ነው?

በ 2019፣ የ Cambridge City Council (የካምብሪጅ ከተማ ምክር ቤት) Cycling Safety Ordinance (CSO) አውጥቷል። ድንጋጌው የከተማውን የአምስት አመት የመንገድ እና የእግረኛ መንገድ እቅድ አካል ሆኖ ጎዳናዎች እንደገና በሚገነቡበት ጊዜ እና በ Bicycle Network Vision (ብስክሌት ኔትወርክ ራዕይ) ውስጥ ለበለጠ መለያየት በተመረጡበት ጊዜ የተነጣጠሉ የብስክሌት መንገዶችን መገንባትን ይጠይቃል።

በ 2020፣ ምክር ቤቱ ለ CSO ማሻሻያዎችን አጽድቋል። ማሻሻያዎቹ በሚቀጥሉት አምስት እና ሰባት ዓመታት ውስጥ ወደ 25 ማይል የሚጠጋ የተለያየ የብስክሌት መንገዶችን ለመትከል የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን አስቀምጠዋል። የእነዚህ ፋሲሊቲዎች መገኛ በሁለቱም በ Cambridge Bicycle Network Vision እና በሕገ ደንቡ ውስጥ የተወሰኑ መስፈርቶችን ያሳውቃል።

ስለ ድንጋጌው እና የፕሮጀክት መረጃ ለበለጠ መረጃ፣ የሚከተለውን ይመልከቱ፡-
https://www.cambridgema.gov/streetsandtransportation/policiesordinancesandplans/cyclingsafetyordinance

## Cycling Safety Ordinance Economic Impact Study

በ2022 ሰመር ላይ፣ የከተማው ምክር ቤት የኢኮኖሚ እድል እና ልማት ክፍል Cycling Safety Ordinance Economic Impact Study እንዲያካሂድ ጠይቋል። በጃንዋሪ 2023፣ ከተማው Cycling Safety Ordinance (CSO) Economic Impact Study ለማካሄድ ከ Volpe ብሔራዊ የትራንስፖርት ስርዓቶች ጋር ስምምነት ተፈራርሟል። ጥናቱ ለሪፖርቱ የሚውለውን የመረጃ አይነት መወሰን፣ መረጃ መሰብሰብ እና ሪፖርት ማዘጋጀትን ያካትታል። ከተማው እና የእኛ አማካሪ መረጃ መሰብሰብ የጀመሩ ሲሆን በ 2023 መገባደጃ ላይ የመጨረሻ ሪፖርት እንጠብቃለን።

በ Economic Impact Study ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ወደ ሚከተለው ድኅረገጽ ይሂዱ፡-
https://www.cambridgema.gov/CDD/Projects/EconDev/cyclingsafetyordinanceeconomicimpactstudy